የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፴፬
አዲስ አበባ – መጋቢት ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፮

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 34
ADDIS ABABA – 21st March 2004

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፩/፲፱፻፺፮ ዓ·ም
የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎች በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣ ደንብ ...................................................... ገጽ ፪ሺ፭፻፺፭

## CONTENTS

Council of Ministers Regulation No. 101/2004 Providing Foreign Nationals of Ethiopian Origin with certain Rights and Privileges to be Exercised in their Country of Origin Regulation ............... Page 2595

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፩/፲፱፻፺፮ የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ ሀገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ ሀገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር ፪፻፸/፲፱፻፺፬ አንቀጽ ፲፯ በተደነገገው መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል ።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ ሀገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣ ደንብ ቁጥር ፩፻፩/፲፱፻፺፮ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ ፤

፩· "አዋጅ" ማለት የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎች በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፪፻፸/፲፱፻፺፬ ነው ።

፪· "የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ ዜጋ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፪(፩) የተሰጠውን ትርጓሜ የሚያሟላ ሰው ማለት ነው ።

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO. 101/2004 A COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOREIGN NATIONALS OF ETHIOPIAN ORIGIN WITH CERTAIN RIGHTS AND PRIVILEGES TO BE EXERCISED IN THEIR COUNTRY OF ORIGIN

This regulation is issued pursuant to the authority vested in the Council of Ministers under Article 5 of Proclamation No. 4/1995 and Article 17 of Providing Foreign Nationals of Ethiopian Origin with certain Rights and Privileges to be Exercised in their Country of Origin Proclamation No. 270/2002.

### PART ONE
### *GENERAL*

1. *Short Title*

This Regulation may be cited as "Providing Foreign Nationals of Ethiopian Origin with Certain Rights and Privileges to be Exercised in their Country of Origin Regulation No. 101/2004."

2. *Definition*

In this regulation unless the context otherwise requires;

1. "Proclamation" means Providing Foreign Nationals of Ethiopian Origin with certain Rights and Privileges to be Exercised in their Country of Origin Proclamation No. 270/2002."
2. "Foreign National of Ethiopian Origin" means a person that falls within the definition provided under Article 2(1) of the Proclamation.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፫· "የኢትዮጵያ ሚስዮን" ማለት የኢትዮጵያ ኤምባሲ ፣ ቋሚ መልዕክተኛ ጽሕፈት ቤት ወይም ቆንስላ ጽሕፈት ቤት ማለት ነው ።

፬· "ሚኒስቴር" ማለት የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማለት ነው ።

፭· "ባለሥልጣን" ማለት የደህንነት ፣ የኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን ማለት ነው ።

፮· በዚህ ደንብ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል ።

## ክፍል ሁለት
## የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎች የመታወቂያ ካርድ

### ፫· የመታወቂያው ካርድ አሰጣጥ ሁኔታ

፩· በዚህ ደንብ መሠረት ለኢትዮጵያ ተወላጅ ለሆነ የውጭ ዜጋ የመታወቂያ ካርድ የሚሰጠው በአዋጁ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች የሚያሟላ እና ከዚህ በታች በተጠቀሰው ሥርዓት መሠረት ማመልከቻ ላቀረበ ሰው ይሆናል።

፪· የመታወቂያ ካርዱን ለማውጣት ማመልከቻ የሚቀርበው በሀገር ውስጥ ለባለሥልጣኑ ሲሆን ከሀገር ውጪ ደግሞ በውጭ በሚገኙ የኢትዮጵያ ሚስዮኖች አማካይነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል ።

፫· ማመልከቻው ለዚሁ ዓላማ በሚኒስቴሩ በተዘጋጀ ቅጽ ተሞልቶና ከሚከተሉት ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል ።

ሀ) በቅርብ ጊዜ የተነሳና ሙሉ ፊትን የሚያሳይ ፎቶግራፍ ፣

ለ) ማመልከቻ አቅራቢው የኢትዮጵያ ተወላጅ መሆኑን የሚያረጋግጡ የሰነድ ማስረጃዎች ፣

ሐ) ዜግነት ካገኘበት አገር አግባብ ካለው አካል የተሰጠ የፀና ፓስፖርት ወይም ሌላ የጉዞ ሰነድ ፣

መ) እንደአግባብነቱ የጋብቻ ማረጋገጫ ሰነድና አሥራ ስምንት ዓመት ያልሞላቸውን ልጆቹን የልደት የምስክር ወረቀት ፣

፬· ሚኒስቴር ወይም ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት ማመልከቻ ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ በ፴ ቀናት ውስጥ የመታወቂያ ካርዱ ለአመልካቹ ሊሰጠው እንደሚገባ ወይም እንደማይገባ መወሰን ይኖርበታል ። የመታወቂያ ካርዱ እንዳይሰጥ የሚወሰን ቢሆን ምክንያቱ ለአመልካቹ በጽሑፍ ሊገለጽ ይገባል ።

### ፬· መታወቂያ ካርዱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፰ መሠረት የተሰጠ መታወቂያ ካርድ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በየአምስት ዓመቱ የሚታደስ ይሆናል ።

፪· የመታወቂያ ካርዱ ዕድሳት በሀገር ውስጥ ሲሆን በባለሥልጣኑ ፣ ከሀገር ውጭ ሲሆን በኢትዮጵያ ሚስዮኖች ሊከናወን ይችላል ።

፫· የመታወቂያ ካርዱ ከመታደሱ በፊት በአዋጁ አንቀጽ ፲፬ መሠረት መታወቂያ ካርዱን ሊያሰርዙ የሚችሉ ምክንያቶች አለመኖራቸው መረጋገጥ አለበት ።

### ፭· ስለ አገልግሎት ክፍያዎች

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፰ መሠረት የሚሰጠውን መታወቂያ ለማግኘት አመልካቹ ፭፻ የአሜሪካን ዶላር /አምስት መቶ የአሜሪካን ዶላር/ ወይም የሚኖርበት አገር ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ ወይም በአገር ውስጥ ሲሆን በወቅቱ የምንዛሪ ዋጋ መሠረት ተመጣጣኝ የሆነ የኢትዮጵያ ብር የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል።

፪· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ መሠረት መታወቂያ ለማሳደስ የሚከፈለው ፪፻ የአሜሪካን ዶላር /ሁለት መቶ የአሜሪካን ዶላር/ ወይም የሚኖርበት አገር ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ ወይም በአገር ውስጥ ሲሆን በወቅቱ የምንዛሪ ዋጋ መሠረት ተመጣጣኝ የሆነ የኢትዮጵያ ብር ይሆናል ።

3. "Ethiopian Mission" means the Ethiopian Embassy, Permanent Representative Office or Consulate;
4. "Ministry" means the Ministry of Foreign Affairs of Ethiopia;
5. "Authority" means the Authority for Security, Immigration and Refugee Affairs;
6. Provisions of this Regulation set out in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

## *PART TWO*
## *Identification Card for Foreign Nationals of Ethiopian Origin*

### 3. *Conditions for Issuance of Identification Card*

1. Under this Regulation, Foreign National of Ethiopian Origin shall be issued with Identification Card provided that he fulfills the provisions of the Proclamation and submits an application in accordance with the procedure set out hereinunder.
2. An application for the issuance of an Identification Card shall be made to the Authority if the applicant is in Ethiopia or to the Ministry through an Ethiopian Mission if the applicant is abroad;
3. An application for an Identification Card shall be made in the prescribed form prepared by the Ministry and shall be accompanied by;
   a) Four recent passport size photographs;
   b) Documentary evidences showing that the applicant is Foreign National of Ethiopian Origin;
   c) A valid passport or another travel document issued by the appropriate body of the country of nationality;
   d) Marriage certificate and birth certificate of his children under the age of 18 if applicable.
4. The Ministry or the Authority, in accordance with this Article shall decide within 30 days from the date of submission of the application whether the Identification Card should be issued to the applicant. When there is a decision not to issue the Identification Card, the reasons for this decision shall be given for the applicant in wrting.

### 4. *Validity of the Identification Card*

1) An Identification Card issued in accordance with Article 8 of the Proclamation shall be renewable every five years since the date of its issuance;
2) The renewal of the Identification Card shall be made by the Authority if the applicant is in Ethiopia and by Ethiopia Missions if the applicant is abroad.
3) Upon the renewal of the Identification Card the renewing authority shall ascertain that the grounds sent out under Article 14 of this Proclamation for canceling the Identification Cared are nonexistent.

### 5. *Service Fees*

1) A fee of US $ 500 (Five Hundred American Dollar) or an equivalent sum of the local currency where the applicant reside or if an applicant is in Ethiopia an equivalent Ethiopian Birr on the basis of the applicable exchange rate shall be payable for the issuance of the Identification Card in accordance with Article 8 of the Proclamation;
2) A fee of US $ 200 (Two Hundred American Dollar) or an equivalent sum of the local currency where the applicant reside or if an applicant is in Ethiopia an equivalent Ethiopia Birr on the basis of the applicable exchange rate shall be payable for the renewal of the Identification Card in accordance with Article 4 of the Regulation.

፫· መታወቂያው የጠፋ ከሆነ መጥፋቱ በአካባቢው ፖሊስ ሲረጋገጥ ወይም የተበላሸ መታወቂያ ለመተካት ፫፻ የአሜሪካን ዶላር /ሦስት መቶ የአሜሪካን ዶላር/ ወይም የሚኖርበት አገር ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ ወይም በአገር ውስጥ ሲሆን በወቅቱ የምንዛሪ ዋጋ መሠረት ተመጣጣኝ የሆነ የኢትዮጵያ ብር በመክፈል ሌላ መታወቂያ ካርድ ሊሰጥ ይችላል ፡፡

፮· <u>የመታወቂያ ካርዱ መያዝ ያለባቸው መረጃዎች</u>

፩· የመታወቂያ ካርዱን የያዘው ሰው ሙሉ ስም ከነአያቱ፣ የተወለደበት ቦታና ቀን ፣ ፆታ ፣ ዜግነትና ልዩ ምልክቶች፤

፪· መታወቂያ ካርዱን የያዘው ሰው በአዋጁ የተጠቀሱት መብቶችና ግዴታዎች እንደሚመለከቱት፤

፫· መታወቂያ ካርዱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ፤

፬· መታወቂያ ካርዱን የሰጠው ባለሥልጣን ፣ የተሰጠበት ቦታና ቀን፤

፭· መታወቂያ ካርዱ ከኢትዮጵያዊ ተወላጅ የውጭ ዜጋ ጋር በተፈጠረ የጋብቻ ግንኙነት የተሰጠ ከሆነ ይኸው በግልጽ መመልከት ይኖርበታል ፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፯· <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ሚኒስቴሩ ይህን ደንብ ለማስፈጸም ዝርዝር መመሪያ ለማውጣት ይችላል ፡፡

፰· <u>ተፈጻሚ ስለማይሆኑ ሕጎች</u>

ይህንን ደንብ የሚቃረኑ ደንቦች ፣ መመሪያዎች ፣ ውሳኔዎች ወይም አሰራሮች ይህን ደንብ በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም ፡፡

፱· <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ጉዳዩ የሚመለከተው መሥሪያ ቤት ወይም ሰው ለዚህ ደንብ ተግባራዊነት የመተባበር ግዴታ አለበት ፡፡

፲· <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል ፡፡

አዲስ አበባ መጋቢት ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

3) Another Identification Card may be issued upon payment of a fee of US $ 300 (Three Hundred American Dollar) or an equivalent sum of the local currency where the applicant reside or if an applicant is in Ethiopia an equivalent Ethiopian Birr on the basis of the applicable exchange rate when the Identification Card is lost, provided that it is confirmed by local police or for the replacement of damaged Identification Card.

6. *Particulars in the Identification Card*

The following particulars shall be clearly specified in the identification card;

1) The full name including the grand father's name, the date and place of birth, sex, nationality and special mark of the holder of the Identification Card;
2) Declaration to the effect that a person holding the Identification card shall be accorded with rights and privileges specified in the Proclamation;
3) The duration of the validity of the Identification Card;
4) The name of Issuing Authority, the place and date of issuance;
5) If the Identification card is obtained on marital relationship with foreign national of Ethiopian origin, declaration to this effect.

## PART THREE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

7. *Power to issue Directives*

The Ministry may issue a directives for the implementation of this Regulation.

8. *Inapplicable Laws*

Any Regulations, directives, decisions or procedural practices shall not apply in so far as they are inconsistent with this regulation.

9. *Duty to Cooperate*

Any concerned institution or individual shall provide the necessary assistance in the implementation of this Regulation.

10. *Effective Date*

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 21st day of March, 2004.

Meles Zenawi
Prime Minister of the Federal
Democratic Republic of Ethiopia